April 8, 2014

# የምስጋና መጎናጸፊያ

እለቱ ሰኞ ነበር፡፡ከስራ አድሬ ቤት የደረስሁት ማለዳ ጧት ነበርና ለአምስት ሰዓታት ገደማ ተኝቼ ነበር ካልጋዬ የተነሳሁት፡፡እንደተነሳሁም ቤት ያፈራውን ቀማምሼ ኮምፒዩተሬ ፊት ካለው ወንበር ላይ ተቀመጥሁ፡በቀደሙት ሰሞናት ያለምኋቸውና ያሰብኳቸው ነገሮች ነበሩ፡፡ተከናወነው አላለቁምና ድንገት ትዝ ብለውኝ በሀይል አስተከዙኝ፡፡ምኑም አልጥመኝ ብሎኝ እጅግ ተጨንቄኛል፡፡መግለጽ የማልችለው ስሜት ከብቦኝና ማስብ አቅቶኝ ደንዝዤ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ዳዊት ይህንን የኔን ስሜት በመዝ 43፡2 ላይ እንዲህ ብሎ ገልጾታል፡-

<<አንተ አምላኬ ሀይሌም ለምን ትተወኛለህ ? ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ?>>

በእንደዚህ አይነት ስሜት ወስጥ ስከበብ የሚታየኝ ነገር መጸለይ ነው፡ነገር ግን መጸለይ አቅቶኛል፤አስጠልቶኛልም፡በቅጽበት አንድ የእግዚአብሔር ሰው የተናገሩት ነገር ትዝ አለኝ፡፡እንዲህ ነበር ያሉት ፡-

<<የመጸለይ ፍላጎት ስታጣና መጸለይ ሲያቅትህ ራስህን ካገኘኸው መጸለይ ያለብህ ያኔ ነው>>

አዎ ትክክል ነበር የተናገሩት፡፡ከሰወየው ሀሳብ ጋር በመስማማት እንደምንም ሸርተት ብዬ ለጸሎት በጉልበቴ ተንበረከክሁ፡የምተነፍሰው ነገር ግን አንደበቴ ላይ አልነበረም፡ለረጅም ጊዜ ጸጥታ ሆነ፡፡ከብዙ ጸጥታ በኋላ አንድ አምልኮ መዝሙር ከፍቼ አብሬ በጸሎት መንፈስ ማዝመርና መፍሰስ ጀመርሁ፡በመህልም በልሳን ረዘም ላሉ ደቂቃዎች መጸለዬን ቀጠልሁ፡እላዬ ላይ የነበረው የከበደኝ ጉም እስኪገፈፍ ላልነሳ ጨክንኩ፡ታምኜ በእምነት እንጂ በማየት ላለመላላስ(2 ቆሮ 5፡6) በመንፈስ አይኖቼን ወደ ጌታዬ አነሳሁ፡ብዙ ሰዓታትን በመቃተት አሳልፌ ለደቂቃ ከተንበረከኩበት ተነስቼ መብራት ላበራ ስል የሆነ ለየት ያለ ቀድሞ ያልነበረ ጉልበትና መታደስ ወደ ወስጤ እንደመጣ ታወቀኝና ደነቀኝ፡፡

ከዚያም ሁኔታው ገርሞኝ የበለጠ እየተነቃቃሁ ለረጅም ጊዜ ጸለይሁ፡ግሩምና ድንቅ የሆነ የተለቀቀ አምልኮና ወዳሴም ወስጥ እራሴን አገኘሁት፡፡ከዚያ የጸሎት ሰአት ጀምሮ ይህንን ሜእክት እስከጻፍኩበት ጊዜ ድረስ የማቋርጥ የዝማሬ፣የደስታና የሰላምን መንፈስን ተጎናጽፈአለሁ፡ይህንን የእኔን ሁኔታ የሚገልጽ ቃል ኢሳ 61፡1-3 ላይ እናገኛለን፡፡እንዲህ ዘርዝሬ ባቀርበው ይፈቀድልኝ፡፡

<<የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው እግዚአብሔር ቀብቶኛልና(ስለ ኢየሱስ አገልግሎት ነውነቢዩ የጻፈልን)፡፡ለመሆኑ ለምንድነው የተቀባው???ሚለሱ እንደሚከተለው ነው፡-

- የተሰበረውን ይጠግን ዘንድ
- ለተማረኩት ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን  ይናገር ዘንድ
- የሚያለቅሱትን ሁሉ ያጽናና ዘንድ
- በአመድ ፋንታ አክሊልን፣በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፤በሃዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ ይሰጥ ዘንድ>>

የከበበኝ ጉም ተበትኖ እና <<በሃዘን ማፈስ ፋንታ የምስጋና መጎናጸፊያ>>ተደርቦልኝ በሚያሟሙ ድንቅ ዝሜዎች ታጅቤ አመሻሹ ላይ ወደ ስራዬ አመራሁ፡፡ለመሆኑ ይህንን ህክምና የት አገኘው ኖሯል?እርሱን የሚወዳደር ሀኪምስ የት ይገኛል?

ዋናው ሚስጥሩ እንዲህ ነው፡ -

ኢሳያስ 12፡3 ላይ <<ወሀወንም ከመድሀኒት ምንጮች በደስታ ትቀዳላችሁ>> እንደሚል በእንደዚህ አይነት ሜበል ወስጥ ስትገቡና ስትዳከሩ፣በነፍሳችሁ ማጋለጥን አቁማችሁ ወደ ጸጋው ዙፋን ኑ(ዕብ 4፡16)፡፡እናም ከዚህ ተዝቆ ከማያልቅ ፋርማሲ መድሀኒታችሁን እፈሱ!!! በመንፈሴ እንጂ በሀይልና በብርታት አይደለም(ዘካ 4፡6) ይላልና!!!

በቀለ በላቸው(ዶ/ር)

240-330-5004

beke_abay@yahoo.com